
# ከቀዶ ጥገና ሕክምና በኋላ
## ለተቀበረ የወንድ ብልት የሚደረግ እንክብካቤ

### የተቀበረ የወንድ ብልት ምንድን ነው?

- አንዳንድ ሕፃናት የተቀበረ የወንድ ብልት ይዘው ይወለዳሉ (ይህን ደግሞ አብሮ የተወለደ እንለዋን)።
- በተጨማሪም የተቀበረ የወንድ ብልት የተደበቀ ብልት፣ የተሸሸገ ብልት፣ የተጣበቀ ብልት ወይም የተጣበቀ የዘር ፍሬ ከረጢት ተብሎ ይጠራል። ይህ በሚሆንበት ጊዜ ብልቱ በከፊል ከቆዳ በታች ይደበቃል።
- ብልቱ በአብዛኛው መደበኛ ርዝመት ያለው ቢሆንም አጭር መስሎ ይታያል። ይህ የሆነበት ምክንያት የሻፍቱ ቆዳ ከብልቱ መነሻ ወለል ጋር ስላልተያያዘ እና የልጅዎ ስብ ንጣፍ ብልቱን ዙሪያውን ስለሚከበው ነው።
- የተቀበረ ብልት ያላቸው አዲስ የተወለዱ ሕፃናት ግርዛት ሲከናወን የብልቱን ሸለፈት ብቻ ሳይሆን በብልቱ ሻፍት ላይ ያለውን ቆዳም ሊያስወግድ ይችላል። ይህ ደግሞ ብልቱ ይበልጥ የተደበቀና ወደ ውስጡ "የተዘረጋ" ሆኖ እንዲታይ ያደርጋል።




የተቀበረ የወንድ ብልት

መደበኛ ብልት ወይም ከቀዶ ጥገና በኋላ ያለው ብልት

### የችግሩ መኖር እንዴት ይታወቃል?

- የልጅዎ ተቀዳሚ ሐኪም ይህንን በመጀመሪያ ሊመለከት እና ወደ ሕፃናት ዩሮሎጂ ባለሙያ ሊመራዎት ይችላል።
- የሕፃናት ዩሮሎጂ ባለሙያው ልጅዎ የተቀበረ ብልት እንዳለው ለማወቅ ቀላል የሆነ የአካል ምርመራ ያደርጋል።

### እንዴት ነው የሚታከመው?

- ልጅዎ በመጠኑ የተቀበረ ብልት ካለው እና ግርዛት የማይፈልጉ ከሆነ ቀዶ ሕክምና ማድረግ ላይኖርብን ይችላል።
- ልጅዎ እያደገ ሲሄድና የስብ ንጣፉ እየጠፋ ሲሄድ ብልቱ ይበልጥ ጎልቶ ሊወጣ (በጣም ጎልቶ ሊታይ) ይችላል።
- ግርዛት እንዲደረግ ከፈለጉና ዶክተሩ የተቀበረ ብልት ካገኙ፣ የግርዛት ሂደቱ የተቀበረውን ብልት በምናስተካክልበት ጊዜ በኦፐሬሽን ክፍል ውስጥ (በክሊኒኩ ውስጥ ሳይሆን) ውስጥ እንዲደረግ ይመክራሉ።
- የተቀበረውን ብልት ማስተካከል በወንድ ብልት መነሻ ወለል ላይ ያለውን ቆዳ ወደታች ማያያዝን (መስፋትን) ያካትታል። ይህም የፔኖ-ፕዩቢክ እና የፔኖ-ስክሮታል መገናኛዎች የበለጠ ግልጽ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል።
- ልጅዎ አስቀድሞ የተገረዘ ከሆነ፣ የቀዶ ጥገናው ሂደት ይበልጥ የተወሳሰበ ሊሆን እና ከሌሎች የሰውነት ክፍሎች ቆዳ ወይም ቲሹ ሊጠቀም ይችላል።



**ተጨማሪ ለማወቅ**

- ዩሮሎጂ
  206-987-2509
- የልጅዎን የህክምና አቅራቢ ይጠይቁ
- seattlechildrens.org

**ነጻ የአስተርጓሚ አገልግሎቶች**

- በሆስፒታል ውስጥ ከሆነ፣ ነርስዎን ይጠይቁ።
- ከሆስፒታል ውጪ ለሆነ ቦታ፣ ወደ ነጻ የቤተሰብ የትርጉም አገልግሎት ስልክ መስመር በ 1-866-583-1527 ላይ ይደውሉ። ለአስተርጓሚዉ የሚፈልጉትን ስም ወይም የውስጥ መስመር ይንገሩ።

Seattle Children's®
HOSPITAL • RESEARCH • FOUNDATION

## ይህን የቀዶ ጥገና ሕክምና ለማድረግ የተሻለው ጊዜ መቼ ነው?

ለሕፃናት የቀዶ ጥገና ሕክምና እንዲደረግ የምንመክረው:-

- ቢያንስ 6 ወር ሲሞላቸው ግን
- ልጅዎ የሽንት ቤት አጠቃቀም ከመልመዱ እና ስለ ጾታ ብልቶቹ ይበልጥ ከማወቁ በፊት።

ሕፃናት ከቀዶ ጥገና ሕክምና በኋላ ከትላልቅ ልጆች በበለጠ ፍጥነት ያገግማሉ።

## ከቀዶ ጥገና ሕክምና በኋላ

### ከቀዶ ጥገና ሕክምና በኋላ ልጄን እንዴት መንከባከብ እንዳለብኝ የሚገልጹ ቪዲዮዎችን የት ማየት እችላለሁ?

ከቀዶ ጥገና ሕክምና በኋላ ልጅዎን እንዴት እንደሚንከባከቡ ለማብራራት ቪዲዮዎችን አዘጋጅተናል። እነዚህን ርዕሶች በYouTube ላይ መፈለግ ይችላሉ። በእድሜ ገደቦች ምክንያት በመለያ መግባት ሊያስፈልግዎት ይችላል።

- “ከዩሮሎጂ ቀዶ ጥገና ሕክምና በኋላ ልጅዎን እንዴት እንደሚንከባከቡ”
  youtube.com/watch?v=epLQn5D62wk
- “ከወንድ ብልት ቀዶ ጥገና ሕክምና በኋላ ልጅዎን እንዴት እንደሚንከባከቡ”
  youtube.com/watch?v=ppZeEKY848M

### ልጄ መቼ ነው መብላት የሚችለው?



- ቀለል ያለ አመጋገብ ይጀምሩ።
- ሕፃናት ከቀዶ ጥገና ሕክምናው በኋላ የሆድ ህመም (ማቅለሽለሽ) የሚሰማቸው ከመሆኑም በላይ ማስመለስ (ትውከት) የተለመደ ነው። ልጅዎን ለመርዳት ቀስ በቀስ ግልጽ የሆነ ፈሳሽ ይስጡት።
- ሙሉ በሙሉ ከእንቅልፉ ሲነቃ፣ ልጅዎ እንደ 7UP፣ Jell-O፣ Popsicles እና የአፕል ጭማቂ ያሉ ግልጽ ፈሳሾችን ሊወስድ ይችላል።
- ልጅዎ የሆድ ሕመም የማይሰማው ወይም የማያስመልስ ከሆነና ሙሉ በሙሉ ንቁ ከሆነ መደበኛ አመጋገቡን ይጀምሩ።

### የቀዶ ጥገና ሕክምናው ለተካሄደበት ቦታ እንክብካቤ የማደርገው እንዴት ነው?



- እስከ 2 ወር ድረስ እብጠት፣ መበለዝ እና ቢጫ ቀለም ያለው ሽፋን ሊኖር ይችላል።
- በቀዶ ጥገና ሕክምናው ወቅት የዩሮሎጂ ባለሙያው ስለ ገላ መታጠብ እና የቁስል መሸፈኛ ጥንቃቄ መመሪያዎች ይሰጥዎታል።

### ልጄ በመታጠቢያ ገንዳ ውስጥ ገላውን መታጠብ፣ ሻወር መውሰድ፣ መዋኘት ወይም ሰውነቱ ማርጠብ ይችላል?



- ከቀዶ ጥገና ሕክምናው በኋላ ልጅዎን በእስፖንጅ ማጠብ ምንም ችግር የለውም። ከቀዶ ጥገና ሕክምናው በኋላ ለ48 ሰዓታት (2 ቀናት) በመታጠቢያ ገንዳ ውስጥ ገላን ከመታጠብ እና ሻወር ከመውሰድ ይቆጠቡ።
- ከ2 ቀናት በኋላ በመታጠቢያ ገንዳ ውስጥ ገላን መታጠብ እና ሻወር መውሰድ ችግር የለውም፣ ነገር ግን ከ10 ደቂቃዎች በላይ ውሃ ውስጥ አይቆዩ።
- ከ2 ቀን የመታጠቢያ ገደቡ በፊት ቢሆንም እንኳን ከሰገራ በኋላ ማጠብ ምንም ችግር የለውም።
- ለ2 ሳምንታት በትላልቅ የውሃ አካላት (የመዋኛ ገንዳዎች፣ ወንዞች፣ ሐይቆች ወይም ውቅያኖሶች) ውስጥ መዋኘት አይፈቀድም።

| | |
|---|---|
| ለቁስል መሸፈኛው (ጥቅም ላይ ከዋለ) ምን ዓይነት እንክብካቤ ማድረግ አለብኝ? | ልጅዎ ከ2 የቁስል መሸፈኛ ዓይነቶች 1 አይነት አለው፡-<br>❑ **ግልጽ የሆነ የቁስል መሸፈኛ፡-** ይህ ከቀዶ ጥገና ሕክምናው በኋላ ከ2 እስከ 10 ቀናት ውስጥ በራሱ ይወድቃል። ይህን ማስወገድ አያስፈልግዎትም።<br>❑ **ነጭ የቁስል መሸፈኛ፡-** የቀዶ ጥገና ሕክምናው ከተደረገ ከ2 ቀናት በኋላ ይህንን በቤት ውስጥ ያስወግዱት። ፋሻው (የቁስል መሸፈኛው) የደም መፍሰስ እና እብጠት አደጋን ለመቀነስ ይረዳል።<br>• የቁስል መሸፈኛው ሊጸዳ በማይችል ቆሻሻ (ሰገራ) በጣም ከቆሸሸ ከቀዶ ጥገና ሕክምናው በኋላ ከ48 ሰዓታት ባነሰ ጊዜ ውስጥ ቢሆንም እንኳን ቆሻሻውን ማጠብ ችግር የለውም።<br>• የቁስል መሸፈኛው ቶሎ ቢወድቅ፣ በቦታው ሌላ አይተኩ። |
| ነጩን የቁስል መሸፈኛ ለማስወገድ፡- | 1. ልጅዎ ለ10 ደቂቃ ያህል በሞቀ የገላ መታጠቢያ ውስጥ እንዲቀመጥ ያድርጉ። ይህን ማድረግዎ የቁስል መሸፈኛውን በማላላት ለማስወገድ ቀላል ያደርገዋል።<br>2. ፋሻው ካልላላ ልጅዎ ለተጨማሪ ከ10 እስከ 20 ደቂቃዎች በመታጠቢያ ገንዳው ውስጥ እንዲቀመጥ ያድርጉ።<br>3. የቁስል መሸፈኛው አሁንም በቀላሉ የማይነሳ ከሆነ ወይም የተጣበቀ የሚመስል ከሆነ 1 ኩባያ ዘይት (በቆሎ፣ የአትክልት፣ የወይራ ወይም የሕፃን ዘይት) በቀጥታ በብልቱ ላይ ያፍስሱ። ይህ ለ20 ደቂቃ ያህል እንዲረስ ይተዉት እና ከዚያ የቁስል መሸፈኛውን ያስወግዱ።<br>የቁስል መሸፈኛው አሁንም የማይነሳ ከሆነ ተጨማሪ ምክሮችን ለማግኘት ወደ ዩሮሎጂ ክሊኒክ ይደውሉ። |
| የፔትሮሊየም ጄሊ (ቫዝሊን) አጠቃቀም | • መጀመሪያ እጆችዎን ይታጠቡ።<br>• በእያንዳንዱ ጊዜ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ መጠን ይጠቀሙ።<br>• በፔትሮሊየም ጄሊ ምትክ አንቲባዮቲክ ቅባት አይጠቀሙ።<br>• ልጅዎ ዳይፐር የሚያደርግ ከሆነ ዳይፐር በሚቀይርበት ጊዜ ሁሉ ይጠቀሙ። ልጅዎ መጸዳጃ ቤት የሚጠቀም ከሆነ በቀን ከ3 እስከ 4 ጊዜ እንዲሁም እንደአስፈላጊነቱ ይጠቀሙ።<br>• ፔትሮሊየም ጄሊውን ለ2 ሳምንታት ወይም ቦታው ሙሉ በሙሉ እስኪድን ድረስ ይጠቀሙ።<br>• የፔትሮሊየም ጄሊውን በንጹህ ጣትዎ ወይም በጥጥ ስዋብ አድርገው ይጠቀሙ።<br>• አስፈላጊ ከሆነ ፔትሮሊየም ጄሊው ሙሉውን ብልት እንዲሸፍን በብልቱ ዙሪያ ያለውን ቦታ (ሱፕራፑቢክ ፋት ፓድ) ወደ ኋላ ይግፉት። |

## ልጄ ማድረግ የሚችለው እንቅስቃሴ ምን ያህል ነው?

- ቀዶ ጥገናው በተካሄደበት ቀን ልጅዎን በቅርበት ይከታተሉ።
- አብዛኛዎቹ ልጆች ከቀዶ ጥገና ሕክምናው በኋላ አንድ ወይም ሁለት ቀን ካለፈ በኋላ ወደ መደበኛ እንቅስቃሴያቸው ይመለሳሉ።

### ልጅዎ እድሜው ከ2 ዓመት በታች ከሆነ፡-



- ትናንሽ ልጆች በራሳቸው መዳህ፣ መራመድ እና እንቅስቃሴዎችን ይገድባሉ።
- የመኪና ውስጥ መቀመጫዎችና የስትሮለር ማሰሪያዎች አስተማማኝ ናቸው። አምራቹ ድርጅት በሚሰጠው መመሪያ መሰረት ይጠቀሙ።
- ለ2 ሳምንታት ያህል በእግሮች መካከል ግፊት እንዲጨምር የሚያደርጉ ማናቸውንም አድካሚ እንቅስቃሴዎችን ከልጅዎ ጋር አያድርጉ።
- የሚከተሉትን አያድርጉ፡-
    - ልጅዎን በወገብዎ ላይ አይያዙ
    - ልጅዎን በጭንዎ ላይ አያዘልሉ
    - የልጆች ማዘያዎችን አይጠቀሙ
    - ባለገመድ ወደ ላይ እና ወደ ታች የሚነቀንቁ መጫወቻዎችን አይጠቀሙ

### ልጅዎ እድሜው 2 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ከሆነ፡-



- ከባድ እንቅስቃሴዎችን፣ አድካሚ የቤት ውስጥ እንቅስቃሴዎችን የሚያካትቱ ተግባራትን ያስወግዱ። በስፋት ተቀባይነት ያለው መርህ ሁለቱም የልጅዎ እግሮች ለ2 ሳምንታት ያህል መሬት ይዘው እንዲቆዩ ማድረግ ነው።
- ልጅዎ ከቀዶ ጥገና ሕክምናው በኋላ ለ2 ሳምንታት ያህል የሚከተሉትን ነገሮች እንዲያደርግ አይፍቀዱለት፡-
    - ጃንግል ጂሞች/መንጠልጠል
    - የጂም ትምህርት
    - ብስክሌት/ባለ ሶስት እግር ብስክሌቶች
    - ከትምህርት ሰዓት በኋላ የሚሰሩ ስፖርቶች

## ልጄ ከቀዶ ጥገና ሕክምናው በኋላ ህመም ይሰማው ይሆን?

- ከቀዶ ጥገና ሕክምናው በኋላ ልጅዎ ብሽሽቱ ላይ ህመም ሊሰማው ይችላል።
- ህመምን በተቻለ መጠን ለማስታገስ ከእርስዎ እና ልጅዎ ጋር አንድ ላይ እንሰራለን። ልጅዎን የበለጠ የሚያውቁት እርስዎ ነዎት። ልጅዎ ማገገም ላይ በንቃት እንዲሳተፉ እናበረታታዎታለን። የልጅዎ የሕመም ስሜት ደረጃ ምንም ያህል ቢሆን፣ የሕመም ስሜቱ እንዳለ በማመን ወዲያውኑ ምላሽ ይስጡ።
- ልጅዎ በሚቀጥለው ቀን ጥሩ ስሜት ሊሰማው ይገባል።

### የልጄን ሕመም መቆጣጠር የምችለው እንዴት ነው?



- ውጤታማ የሆነ የሕመም ቁጥጥር ልጅዎ የተሻለ ስሜት እንዲሰማው እና ቶሎ እንዲያገግም ያደርጋል። ከቀዶ ጥገና ሕክምናው በኋላ ባሉት የመጀመሪያዎቹ 2 ቀናት ለልጅዎ አሲታሚኖፌን (ታይሌኖል) እና አይቢዩፕሮፌን (አድቪል ወይም ሞትሪን) በየ3 ሰዓቱ በማለዋወጥ በመስጠት ይጀምሩ እና ከዚያ እንደአስፈላጊነቱ ይጠቀሙበታል። ለልጅዎ ማንኛውንም ዓይነት መድሃኒት ከመስጠትዎ በፊት የህክምና አገልግሎት አቅራቢን ያማክሩ።
- የልጅዎ የህክምና አገልግሎት አቅራቢ ለህመም የሚሆን ኦፒዮይድ መድሃኒት ካዘዘ፣ አሲታሚኖፌን ወይም አይቢዩፕሮፌን ህመምን ለማስታገስ ካልረዱ ያንን ይጠቀሙ።
- ታይሌኖል እና በሐኪም የታዘዙ የህመም ማስታገሻ መድሃኒቶች በተመሳሳይ ጊዜ መጠቀም አደገኛ ሊሆን ይችላል። የሕክምና አገልግሎት አቅራቢዎን ወይም ፋርማሲ ያማክሩ።
- ከህመም ማስታገሻ መድሃኒት በተጨማሪ ልጅዎን በሙዚቃ፣ በጨዋታዎች፣ በመጻሕፍት፣ በቴሌቪዥን ወይም በቪዲዮዎች እንዲዝናኑ በማድረግ ህመሙን እንዲቋቋም ሊረዱት ይችላሉ።

## የተረፈ ኦፒዮይድ የህመም ማስታገሻ መድሃኒትን እንዴት ማስወገድ እችላለሁ?

- የእርስዎን ቤተሰብ ደህነንት ለመጠበቅ፣ መድሃኒቶችን ሌሎች በቀላሉ ማግኘት በማይችሉበት ቦታ ወይም በተቆለፈ ካቢኔት ውስጥ ያስቀምጡ። ልጅዎ አንድ ጊዜ ከቀዶ ጥገና ሕክምናው ካገገመ በኋላ፣ ሁሉንም ጥቅም ላይ ያልዋሉ የታዘዙ መድሃኒቶችን ያስወግዱ።
- የተረፈ የህመም ማስታገሻ መድሃኒትን ወይም ሌሎች መድሃኒቶችን ሆን ብሎ ወይም በአጋጣሚ መውሰድ በጣም አደገኛ ሊሆን ይችላል።
- ጥቅም ላይ ያልዋሉ ኦፒዮይድ መድሃኒቶችን ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ እንዴት ማስወገድ እንደሚቻል ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት "የኦፒዮይድ መድሃኒቶች ደህንነቱ የተጠበቀ አጠቃቀም እና አወጋገድ" (seattlechildrens.org/pdf/PE3140.pdf) የተሰኘውን የመረጃ ጽሁፍ ያንብቡ ወይም በአቅራቢያዎ የሚገኝ የመመለሻ ቦታን ለማግኘት takebackyourmeds.orgን ይጎብኙ።

## ልጄ ወደ ትምህርት ቤት መመለስ የሚችለው መቼ ነው?

ልጅዎ ኦፒዮይድ የህመም ማስታገሻ መድሃኒት ወይም በቀን ውስጥ በተደጋጋሚ ያለ ሃኪም ማዘዣ የሚሰጥ የህመም ማስታገሻ መድሃኒት በማይፈልግበት ጊዜ ወደ ትምህርት ቤት ሊመለስ ይችላል። የትምህርት ቤቱ ነርስ ፔትሮሊየም ጄሊውን በልጅዎ ብልት ላይ ለማድረግ ፍቃደኛ መሆን እንዳለባት ወይም ልጅዎ በራሱ ማድረግ እንደሚያስፈልገው ልብ ይበሉ።

## መቼ ነው የምደውለው?

ለጥያቄዎች ወይም ከዚህ በታች ለተዘረዘሩት ስጋቶች ከሰኞ እስከ አርብ ለዩሮሎጂ ክሊኒክ በ206-987-2509 በመደወል መጠየቅ ይችላሉ። አስቸኳይ ላልሆኑ ጥያቄዎች በ MyChart መልዕክቶች ይላኩ።

በምሽት፣ ቅዳሜና እሁድ እንዲሁም በበዓላት፣ በ206-987-2000 ይደውሉ እና ከሚከተለው ዝርዝር ውስጥ ለድንገተኛ ጉዳዮች ተረኛ የዩሮሎጂ ባለሞያን በስልክ ይጠይቁ፡

- በደም የተለወሰ ዳይፐር ወይም የውስጥ ልብስ - ያለማቋረጥ ደም እየፈሰሰ ከሆነ ለ5 ደቂቃዎች ግፊት ያድርጉ እና ለድንገተኛ እርዳታ ክፍል በ206-987-2222 ይደውሉ።
- መቅላት፣ ቀለም መቀየር፣ መበለዝ፣ እብጠት ወይም ከቀስሉ ላይ መግል (ፈሳሽ) ወውጣት
- ቀዶ ጥገናው የተካሄደበት ቦታ በፍጥነት ካበጠ ወይም ደም ከፈሰሰ
- በሐኪም የታዘዘው መድኃኒት የማይቆጣጠረው ከባድ፣ የማያቋርጥ ህመም
- ከ24 ሰዓት በላይ ለሆነ ጊዜ ከ101.5°F (38.6°C) በላይ የሆነ ትኩሳት
- ከቀዶ ጥገና ሕክምናው በኋላ ለ8 ሰዓታት ያህል መሽናት ካልቻለ
- በ12 ሰዓታት ውስጥ 4 ወይም ከዚያ በላይ ጊዜ ማስመለስ (ማስታወክ)

Seattle Children's መስማት ለተሳናቸዉ፣ መስማት ለሚቸገሩ ወይም ከእንግሊዝኛ የተለየ ቋንቋ ለሚናገሩ ታካሚዎች፣ የቤተሰብ አባላትና የህግ ተወካዮች፣ ነጻ የአስተርጓሚ አገልግሎቶች ይሰጣል። በጥያቄ መሰረት Seattle Children's ይህን መረጃ በአማራጭ ፎርማቶች እንዲገኝ ያደርጋል። ለቤተሰብ ሃብት ማዕከል በ 206-987-2201 ላይ ይደዉሉ። ይህ የመረጃ መስጫ ጽሁፍ በSeattle Children's ክሊኒካል ሰራተኞች ተገምግሟል። ነገር ግን፣ የእርስዎ ፍላጎቶች ልዩ ናቸዉ። ወደተግባር ከመግባትዎ ወይም በዚህ መረጃ ላይ ከመደገፍዎ በፊት፣ እባክዎ የእርስዎን የጤና እንክብካቤ ሰጪ ያነጋግሩ።

8/22
PE2734AM


© 2023 Seattle Children's, Seattle, Washington. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነዉ።

# Buried Penis

## Care After Surgery

### What is a buried penis?

- Some babies are born with a buried penis (we call this congenital).
- A buried penis is also called hidden penis, concealed penis, webbed penis or webbed scrotum. When this happens, the penis is partly hidden below the skin.
- The penis is usually normal length but appears shorter. This is because the shaft skin is not attached at the base of the penis and your baby's fat pad surrounds the penis.
- Newborn circumcisions done on babies with buried penis can remove some of the skin on the shaft of the penis, instead of just the foreskin. This makes the penis appear even more hidden and "telescope" inward.




### How is it diagnosed?

- Your child's primary care provider may first notice this and refer you to a pediatric urologist.
- The pediatric urologist will do a simple physical exam to see if your child has a buried penis.

### How is it treated?

- If your child has a mild form of a buried penis and you do not want a circumcision, we may not need to do surgery.
- As your baby gets older and the fat pad disappears, the penis may stick out more (become more prominent).



**To Learn More**

- Urology
  206-987-2509
- Ask your child's healthcare provider
- **seattlechildrens.org**

**Free Interpreter Services**

- In the hospital, ask your nurse.
- From outside the hospital, call the toll-free Family Interpreting Line, 1-866-583-1527. Tell the interpreter the name or extension you need.

Seattle Children's®
HOSPITAL • RESEARCH • FOUNDATION

- If you desire a circumcision and the doctor finds a buried penis, they will recommend doing the procedure in an operating room (not at the clinic) at the same time we repair the buried penis.
- Repairing a buried penis includes tacking (suturing) the skin down at the base of the penis. This will cause the peno-pubic and peno-scrotal junctions to be more defined.
- If your baby was already circumcised, the surgery may be more involved and use skin or tissue from other parts of the body.

### When is the best time for this surgery?

We recommend surgery for babies:

- When they are at least 6 months old but
- Before your child is potty trained and becomes more aware of their genitals.

Babies tend to recover faster than older children from surgery.

## After surgery

### Where can I watch videos that explain how to care for my child after surgery?

We created videos to explain how to care for your child after surgery. You can search for these titles on YouTube. You may need to login due to age restrictions.

- "How to Care for Your Child After Urologic Surgery"
  **youtube.com/watch?v=epLQn5D62wk**
- "How to Care for Your Child After Penile Surgery"
  **youtube.com/watch?v=ppZeEKY848M**

### When can my child eat?

- Start with a light diet.
- It is common for children to feel sick to their stomach (have nausea) and throw up (vomit) after surgery. Slowly give your child clear liquids to help.
- When fully awake, your child may have clear liquids like 7UP, Jell-O, Popsicles and apple juice.
- If your child is not sick to their stomach or throwing up and is fully awake, start their regular diet.

### How do I care for the surgery site?

- Expect swelling, bruising, and yellow film for up to 2 months.
- Your urologist will give you instructions on bathing and dressing care at the time of surgery.

## Can my child take a bath, shower, swim or get wet?



- It is ok to sponge bathe your child after surgery. Avoid showers and baths for 48 hours (2 days) after surgery.
- It is ok for showers or baths after 2 days, but do not soak for longer than 10 minutes.
- It is ok to rinse off poop even if it is before the 2-day bath cutoff.
- No swimming in large bodies of water for 2 weeks (pools, rivers, lakes or oceans).

## How do I care for the dressing (if used)?

Your child has 1 of 2 types of dressing:

- ❑ **Clear dressing**: this will fall off on its own some time from 2 to 10 days after surgery. You do not need to remove this.
- ❑ **White dressing**: remove this 2 days after surgery at home. The bandage (dressing) helps to reduce the risk of bleeding and swelling.
  - If the dressing becomes very dirty with poop (stool) that cannot be wiped off, it is ok to rinse off poop even if it is less than 48 hours after surgery.
  - If the dressing falls off early, do not replace it.

## To remove the white dressing:

1. Have your child sit in a warm bath for about 10 minutes. This helps loosen the dressing and makes it easier to remove.
2. If the bandage is not loosening, have your child sit in the bath for another 10 to 20 minutes.
3. If the dressing is still not coming off easily or seems to be stuck, apply 1 cup of oil (corn, vegetable, olive or baby oil) directly on the penis. Allow this to soak in for 20 minutes and then remove the dressing.

   If the dressing is still not coming off, call the Urology clinic for more tips.

## Tips for using petroleum jelly (Vaseline)

- Wash your hands first.
- Use a moderate to large amount each time.
- Do not use antibiotic ointment instead of the petroleum jelly.
- If your child is in diapers, apply it at every diaper change. If your child uses the toilet, apply it 3 to 4 times a day and as needed.
- Use the petroleum jelly for 2 weeks or until the area is completely healed.
- Put the petroleum jelly on with your clean finger or cotton swab.
- Push back the area around the penis (suprapubic fat pad) if needed so that the petroleum jelly covers the entire penis.

## How much activity can my child do?

- Watch your child closely on the day of the surgery.
- Most children will return to regular activity a day or two after surgery.

### If your child is younger than 2 years of age:



- Younger children will limit their own crawling, walking and activities.
- Car seats and stroller straps are safe. Use as instructed by the manufacturer.
- Avoid any straddle activities with your child that would increase pressure between the legs for 2 weeks.
- Do not:
  - Hold your child on your hip
  - Bounce your child on your knee
  - Use baby-wearing devices
  - Use bouncer toys that have a harness

### If your child is 2 years of age or older:



- Avoid strenuous activities, rough-housing or activities that involve straddle-activity. A good rule of thumb is to keep both of your child's feet on the ground for 2 weeks.
- **Do not let your child do the following for 2 weeks after surgery:**
  - Jungle-gyms/climbing
  - Gym class
  - Bicycle/tricycles
  - After-school sports

## Will my child have pain after surgery?

- After surgery, your child will likely feel pain in the groin.
- We partner with you and your child to relieve pain as much as possible. You know your child best. We encourage you to take an active part in your child's recovery. No matter the level of your child's pain, believe they are hurting and respond right away.
- Your child should feel better the next day.

### How do I manage my child's pain?



- Effective pain control will help your child feel better and heal faster. Start by giving your child acetaminophen (Tylenol) alternating every 3 hours with ibuprofen (Advil or Motrin) for the first 2 days after surgery and then you will use it as needed. Check with the healthcare provider first before giving any type of medicine to your child.
- If your child's healthcare provider prescribed an opioid medicine for pain, use this if the acetaminophen or ibuprofen does not help relieve pain.
- Tylenol and prescription pain medicine may not be safe to use at the same time. Check with your healthcare provider or pharmacy.
- In addition to medicine for pain, you can also help your child cope by distracting them with music, games, books, TV or videos.

### How do I dispose of leftover opioid pain medication?

- To keep your family safe, store medicines inside a locked cabinet or location where others cannot easily get to them. Once your child has recovered from surgery, dispose of all unused prescription medicines.
- Taking leftover pain or other medicines, on purpose or by accident, can be very dangerous.
- For more information about safe disposal of unused opioid medicine, read our handout "Safe Use and Disposal of Opioid Medicines" (**seattlechildrens.org/pdf/PE3140.pdf**) or visit **takebackyourmeds.org** to find a take-back place near you.

## When can my child return to school?

Your child may return to school when they no longer need opioid pain medicine or frequent daytime over-the-counter pain medications. Keep in mind the school nurse will need to be comfortable with putting the petroleum jelly on your child's penis or your child will need to do it.

## When do I call?

Monday to Friday, call the Urology Clinic at **206-987-2509** for questions or any of the concerns listed below. Send MyChart messages for non-urgent questions.

Nights, weekends and holidays, call **206-987-2000** and ask for the urology resident on call for urgent concerns from the following list:

- Blood-soaked diaper or underwear - apply pressure for 5 minutes if actively bleeding and call the Emergency Department at **206-987-2222**.
- Redness, discoloration, bruising, swelling or discharge (fluid) from the wound
- Rapid swelling or bleeding at the site of surgery
- Severe, constant pain not controlled by the medicine prescribed
- Fever higher than 101.5° F (38.6° C) for more than 24 hours
- Cannot pee for a span of 8 hours after surgery
- Throwing up (vomiting) 4 or more times in 12 hours

Seattle Children's offers free interpreter services for patients, family members and legal representatives who are deaf or hard of hearing or speak a language other than English. Seattle Children's will make this information available in alternate formats upon request. Call the Family Resource Center at 206-987-2201. This handout has been reviewed by clinical staff at Seattle Children's. However, your needs are unique. Before you act or rely upon this information, please talk with your healthcare provider.

© 2022 Seattle Children's, Seattle, Washington. All rights reserved.

8/22
PE2734